Hamlin Fistula Ethiopia

# ሐምሊን ዜና መጽሔት

ቁጥር 5 ፤ ሚያዝያ 2010 ዓ.ም.

**በሐምሊን ፌስቱላ ኢትዮጵያ በየሦስት ወሩ እየተዘጋጀ ለሠራተኞቹ የሚሰራጭ**



## በአገራችን በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነው የዩሮጋይኒኮሎጂ ሳብስፔሻሊቲ ተመራቂዎች

**ዶ/ር ፈቃደ አየናቸው እና ዶ/ር መላኩ አብርሃ**

**በውስጥ ገፆች**


- የዩሮጋይኒኮሎጂ የመጀመሪያዎቹ ተመራቂዎች 2
- አዲስ ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚ 4
- የሴቶች ቀንን በፅዳት 5
- የአልትራሳውንድ ስልጠና 7
- የሐምሊን ሁሉን አቀፍ ህክምና ማሳያ ስፍራ 8
- የመቱ ሐምሊን ፌስቱላ ማዕከል 10

# የዩሮጋይኒኮሎጂ ሳብስፔሻሊቲ የመጀመሪያዎቹ ሰልጣኞች ተመረቁ



በአገራችን በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነውና በሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ፣ በመቐለ ዩኒቨርሲቲና በአለም አቀፍ የፊስቱላ ፋውንዴሽን ጥምረት እየተሰጠ የሚገኘውን የሦስት ዓመት የዩሮጋይኒኮሎጂ ሳብስፔሻሊቲ ስልጠናን ያጠናቀቁ የመጀመሪያዎቹ ሰልጣኞች ዶ/ር ፈቃደ አየናቸው ከዋናው የፊስቱላ ሆስፒታል እና ዶ/ር መላኩ አብርሃ ከመቀሌ ሐምሊን ማዕከል መጋቢት 1፣ 2010 ዓ.ም በመቐለ ዩኒቨርሲቲ በተደረገው ስነ ስርዓት ተመረቁ፡፡

ዩኒቨርሲቲው በዕለቱም በተለያዩ የጤና ሳይንስ መስኮች ያሰለጠናቸውን 358 ተማሪዎችን አስመርቋል፡፡

በምረቃው ስነስርዓት የተከበሩ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ፕሮፌሰር ይፍሩ ብርሃን፣ የመቐለ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ፕሮፌሰር ክንደያ ገ/ህይወት፣ የዩኒቨርሲቲው የሴኔት አባላት፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ አገር የተጋበዙ እንግዶች፣ የተመራቂ ቤተሰቦችና የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አባላት ተገኝተዋል፡፡

በስነስርዓቱ ላይ ተመራቂዎቹንና የተመራቂ ቤተሰቦችን እንኳን ደስ ያላችሁ በማለት ንግግራቸውን የጀመሩት የመቐለ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ፕሮፌሰር ክንደያ ገ/ህይወት፣ ተመራቂዎቹ አገርቱ የጣለችባቸውን ሃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡም ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡ “የለውጣችን ትልቁ ስትራቴጂ ማዳመጥ፣ ማገናዘብና መተግበር ሲሆን እነኚህን ደግሞ

በዩኒቨርሲቲው ቆይታችሁ ሙሉ በሙሉ እንዳዳበራችሁ እርግጠኛ ነኝ፡፡ በቀጣዩ ተግባራችሁ በቆይታችሁ ያገኛችሁትን ዕውቀትና ክህሎት ለአገራችሁ በሙሉ ቅንነት እንድታደረሱ አደራ እላችኋለሁ” ብለዋል፡፡

በስነ ስርዓቱም ለዩሮጋይኒኮሎጂ ሳብስፔሻሊቲ ስልጠና ትልቅ አስተዋጽኦ ላበረከቱት ለፕሮፌሰር ክንደያ ገ/ህይወት፣ ለፕሮፌሰር ሊዊስ ዎል፣ ለዶ/ር ሬናታን ሮንገን፣ ለዶ/ር ካረን ጎልድ እና ለዶ/ር አማኑኤል አይሌ



የዕለቱ የክብር እንግዳ የተከበሩ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ፕሮፌሰር ይፍሩ ብርሃን በበኩላቸው ተመራቂዎችንና የተመራቂ ቤተሰቦችን እንኳን ደስ ያላችሁ ብለዋል፡፡ “በመሃላችሁ በመገኘቴ ትልቅ ደስታ ተሰምቶኛል፡፡ ዛሬ ለእናንተና ለቤተሰቦቻችሁ ትልቅ ቀን ነው፤ ለዓመታት የደከማችሁለት ፍሬ አፍርቶ ያያችሁበት በመሆኑ፡፡ …. በዚህ አጋጣሚ ላስታውሳችሁ የምፈልገው ቀጣይ የስራ ዘመናችሁን በጥንካሬ እንድትወጡ ነው፡፡ ጠንካሮች ስትሆኑ እንደ ግለሰብ ብሎም እንደ አገር ያቀዳችሁትን በቀላሉ ታሳካላችሁ፤በጤና ዘርፍም የምታበረክቱት አስተዋጽኦም የላቀ ይሆናል” በማለት መልካም ምኞታቸውን ገልጸዋል፡፡

በዶ/ር ካትሪን ሐምሊንና በዶ/ር ተስፋዬ ያዕቆብ የተፈረመ የምስጋና ሰርተፊኬት በሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ስም ተበርክቶላቸዋል፡፡

በመላው አፍሪካ በዘርፉ ጠንካራ የትምህርት፣ የህክምና እንዲሁም የጥናትና ምርምር ማዕከል መፍጠርን ራዕዩ ያደረገው የስልጠና ፕሮግራሙ አስቀድመው በሙያው የካበተ ልምድ ያላቸው ሃኪሞችን ተቀብሎ ለሶስት አመታት በማሰልጠን ከተለመደው ወጣ ያሉና ውስብስብ ችግሮችን የማከም አቅምን በመፍጠር በዘርፉ እንደሃገር የሚታየውን የባለሙያ እጥረት እንደሚቀርፍ ይገመታል፡፡

# አዲስ የሐምሊን ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚ

አቶ ተስፋዬ ማሞ ይባላሉ፡፡ በጤናው ዘርፍ በተለይም በሆስፒታል አስተዳደር ዓመታትን የተሻገረ ሰፊ ልምድ አላቸው፡፡ በቅርቡ ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ለምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚ መደብ ባወጣው ይፋዊ የስራ ማስታወቂያ አማካኝነት ተወዳድረው በየደረጃው የቀረቡ መመዘኛዎችን በማሟላት ብቁ ሆነው ተመርጠዋል፡፡ ከሚያዝያ 2010 ዓ.ም ጀምሮም የሐምሊን ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚ በመሆን መደበኛ ስራቸውን ጀምረዋል፡፡

በተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ያካበቱትን ከ20 ዓመታት በላይ የአስተዳደር ልምድ ይዘው የሐምሊንን ማናጅመንት ቡድን የተቀላቀሉት አቶ ተስፋዬ ከቡድኑ አባላት ጋር በጋራ በመሆን የሐምሊንን መደበኛና ስትራቴጂያዊ ተግባራት እንደሚያፋጥኑ ይጠበቃል፡፡ የተረከቡትን ኃላፊነት አስመልክተው በሰጡት አስተያየትም፣ “የድርጅቱ ከፍተኛ የቦርድ አባላትና ዋና ስራ አስፈፃሚ ለጣሉብኝ እምነት ከፍተኛ አክብሮት አለኝ፡፡ እራሴን በሐምሊን የተጀመረው የስትራቴጂያዊ ለውጥ አንድ አካል ሆኜ ከመላው ሠራተኛ ጋር የድርጅቱን አንጋፋነትና የወሊድ ፊስቱላ ጉዳትን በማከምና በመከላከል ተግባር በአለም አቀፍ ደረጃ ያገኘውን ተቀባይነት ማስቀጠል እንዲሁም በዘርፉ ለመላው ዓለም የልህቅ ማዕከል ለማድረግ እሰራለሁ” ብለዋል፡፡

በትምህርት ዝግጅታቸው ከማናጅመንት እና አመራር ሰጪነት ጋር የተያያዙ



ሁለት የማስተርስ ዲግሪዎችን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና ከእንግሊዙ ግሪንዊች ዩኒቨርሲቲ የተቀበሉት አቶ ተስፋዬ የምርምርና ጥናት ሥራዎቻቸው በጤና ማናጅመንት እና ኢኮኖሚክስ ዘርፍ ሆኖ የሆስፒታል አመራር፣ የህክምና አግልግሎት ጥራት፣ የታካሚዎች እርካታና ፍሰት ማሳለጥ ላይ ያተኩራል፡፡ አቶ ተስፋዬ ሐምሊንን ከመቀላቀላቸው በፊት የተዘንአ አጠቃላይ ሆስፒታል ስራ አስኪያጅ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የህክምና ሳይንስ ኮሌጅ ስራ አስኪያጅ እንዲሁም በአ.አ.ዩ ህክምና ትምህርት ክፍል በዲንነትና በአስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊነት ያላቸው የስራ ልምዶች ተጠቃሾቹ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ለበርካታ ዓመታት የቀይ መስቀል ከፍተኛ አመራር አባል ሆነው ሰርተዋል፡፡

መላው የሐምሊን ሠራተኛ እና የማናጅመንት ቡድን አባላት አዲሱን ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ተስፋዬን የሐምሊንን ቤተሰባዊ የስራ ከባቢ በመቀላቀላቸው እንኳን ደስ አለዎ እያለ መልካም የስራ ዘመን እንዲሆንላቸውም ተመኝቷል፡፡

# የሴቶች ቀንን በፅዳት



የዘንድሮው ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን **“ጊዜው አሁን ነው-የገጠርና ከተማ ተግባራት ለሴቶች ህይወት ለውጥ”** በሚል መሪ ሀሳብ በመላው ዓለም ተከብሮ ውሏል፡፡ ዕለቱን በማስመልከት የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ዋናው መስሪያ ቤት ሠራተኞች የስራ ቦታቸውን በዘመቻ በማፅዳት አክብረው ውለዋል፡፡

በድርጅቱ ሜትረን ሲስተር ውዴ መሪነት በጠዋቱ የተጀመረው የፅዳት ዘመቻ በእለቱ በስራ ላይ የነበሩና ከሁሉም የስራ ክፍሎች የተውጣጡ ከ100 በላይ ሠራተኞችን ያሳተፈ ነበር፡፡

በዘመቻው በመደበኛው ዕለታዊ የፅዳት ስራ ያልተሸፈኑ አንዳንድ ቦታዎች ፀድተው ለታካሚዎች አገልግሎት እንዲሰጡ ሆኗል፡፡

ሐምሊን በሴቶች ለሴቶች የሚሰራ ምናልባትም በአገር ደረጃ የሴት ሠራተኞች ቁጥር ከወንዶች በእጅጉ ልቆ የሚታይበት ብቸኛው ተቋም እንደመሆኑ አስቀድሞ የስርዓተ ፆታ እኩልነትን ያረጋገጠ ድርጅት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ የክብረ በዓሉ አስተባባሪ ሲስተር ውዴም ይህንኑ በማጠናከር ሐምሊን የሴቶች ድርጅት እንደመሆኑ ሠራተኞቹ የዘንድሮውን ዓለም አቀፉን የሴቶች ቀን በፅዳት

ዘመቻ ሲያከብሩ አንድም በሐምሊን ለዘመናት ሲሰራበት የቆየውን ሴቶችን ማዕከል ያደረገ የስራ ከባቢን ለማመስገን በሌላ በኩል ተምሳሌታዊነቱ በአገር ደረጃ እንዲታይ የበለጠ ለመስራት ቃል ለመግባት ነው ብለዋል፡፡ ክብረ በዓሉ በመጨረሻም በፅዳት ዘመቻው የተሳተፉ ሠራተኞች የተገኙበት የሻይ ቡና ስነ ስርዓት ተካሂዶ ተጠናቋል፡፡

ከዚሁ የፅዳት ዘመቻ ጋር በተያያዘ የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ማናጅመንት ለመላው የዋና መስሪያ ቤት ሠራተኞች መልዕክት አስተላልፏል፡፡ በመልዕክቱም በቅርቡ በተጀመረው የቢሮ ግንባታ ምክንያት ቀደም ሲል የግቢያችን ውበት አካል የነበሩ ጥቂት ቦታዎች የተነሱ ቢሆንም አብዛኛው የአረንጓዴ መስክ ግን ግንባታው የማይደርስበት በመሆኑ አሁንም ውበቱን ጠብቆ ይገኛል፡፡ በመሆኑም መላው ሠራተኛ በሴቶች ቀን እንዳደረገው ሁሉ በየዕለቱ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ለግቢው ውበት የተለመደውን ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡ በሳር ላይ መሄድና አበባ መቁረጥ ከመሳሰሉ ተግባራት በመቆጠብ አትክልተኞችን ማገዝና የስራ አካባቢያችንን እንደሁልጊዜው ሁሉ ውብ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ ይገባናል ብሏል ማናጅመንቱ፡፡



# ሐምሊን በጤና ጣቢያዎቹ የአልትራሳውንድ ምርመራ አገልግሎት ሊጀምር ነው

የሐምሊን ሚድዋይፈሪ ኮሌጅ ከአምስቱ የሐምሊን የቅርንጫፍ ማዕከላት ለተውጣጡ ሜንተሮችንና የሚድዋይፈሪ ሙያ ላላቸው ለኮሌጁ መምህራን በድምሩ 10 ሰልጣኞች በኢትዮጵያ የራዲዮሎጂ ማህበር በተመረጡ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን በአልትራሳውንድ ምርመራና አጠቃቀም ላይ ያተኮረ ስልጠና ሰጠ።

የሐምሊን ሚድዋይፈሪ ኮሌጅ ዲንና የድርጅቱ መከላከል ፕሮግራም ኃላፊ አቶ ዘላለም በለጠ እንዳሉት ተቋሙ በመከላከል ፕሮግራሙ በተመረጡ ገጠራማ አካባቢዎች ለሚገኙ ከአርባ በላይ የመንግስት ጤና ጣቢያዎች ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በማድረግ የአካባቢው እናቶች ጥራት ያለው የወሊድ፣ ቅድመ ወሊድና ድህረ ወሊድ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ላይ ይገኛል። የጤና ጣቢያዎቹን የእናቶች ጤና አገልግሎት ደረጃ ከፍ የሚያደርጉ የቁሳቁስ፣ የመድሃኒቶች፣ የክፍሎች ግንባታና እድሳት የመሳሰሉት ድጋፎችን ለአብነት ያስታወሱት አቶ ዘላለም አሁን ደግሞ በቀላሉ መንቀሳቀስ በሚችሉ የአልትራሳውንድ መሳሪያዎች በመታገዝ አገልግሎቱን በጤና ጣቢያ ደረጃ ለመጀመር ዝግጅት መጠናቀቁን ገልፀዋል። በኢትዮጵያ የራዲዮሎጂ ማህበር በኩል የተሰጠው ስልጠናም የዝግጅቱ አካል እንደሆነ አስታውሰዋል።

ለ10 ተከታታይ ሳምንታት የቆየው ይህ ስልጠና የፅንሰ-ሀሳብና የተግባር ልምምድ ያካተተ ሲሆን እያንዳንዱ ሰልጣኝ ብቁ የሚሆነው 160 ነፍሰጡር እናቶችን በቀላሉ በሚንቀሳቀስ የአልትራሳውንድ መሳሪያ መርምሮ ውጤቱ ከታየ በኋላ እንደሆነ አቶ ዘላለም ገልጸዋል።

የአልትራሳውንድ አገልግሎት በጤና ጣቢያ ደረጃ መጀመሩ ሚድዋይፎች ከወሊድ ጋር የተያያዙ ችግሮችን በቀላሉና በፍጥነት መለየት እንዲችሉ ከማስቻሉም በላይ የእናቶችና ህፃናት ሞት በመቀነስ ረገድ ከፍ ያለ ሚና እንደሚኖረው አቶ ዘላለም አስታውቀዋል።



## ደስታ መንደር ---

## የሐምሊን ሁሉን አቀፍ ህክምና ማሳያ ስፍራ



ባሳለፍነው ታህሳስ ወር ሌሎች ስምንት ከከፍተኛ የፊስቱላ ጉዳት ያገገሙ ታካሚዎች የደስታ መንደር ሁሉን አቀፍ የህይወት ክህሎት ስልጠናቸውን አጠናቀው የ16ኛው ዙር ተመራቂዎች ሆኑ፡፡ ከአስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት መጠናቀቅ በኋላ ከየመጡበት ማህበረሰብ ጋር እንዲቀላቀሉ ሲደረግ ደግሞ በእነሱ እግር ሌሎች መሰል ተጎጂዎች ተተክተው ስልጠናቸውን በመከታተል ለቀጣይ ምርቃት ራሳቸውን ያሰናዳሉ፡፡ ቀጥሎ ደግሞ ሌሎች፤ ከዚያም እነደዚሁ ... ይህ ነው እንግዲህ የደስታ መንደር ዋነኛ ተልዕኮ፡፡

ከ 10 ዓመታት በፊት ደስታ መንደር ሲመሰረት ዓላማው ከባድ ጉዳት አጋጥሞዋቸው የተለየ ህክምና ያገኙና በጉዳቱ ሰበብ ወደ መጡበት ተመልሰው መደበኛ ህይወት መምራት ይቸገራሉ የተባሉ የፊስቱላ ተጎጂዎች መኖሪያ ተደርጎ ሲሰራ የቆየው፡፡ በጊዜ ሂደት በተደረገ ምልከታ ይህ ዓይነቱ አካሄድ የማያዛልቅና ከታካሚዎቹ አኳያም ጥገኝነትን ማበረታታት ሆኖ በመገኘቱ የአቅጣጫ ለውጥ ተደረገ፡፡

በመሆኑም ደስታ መንደር ከሐምሊን ሦስቱ ዋና የስራ ዘርፎች አንዱ ሆኖ የማገገሚያና መልሶ ማቋቋሚ በሚል አስቀድሞ በሚደረግ የተናጠል ልየታ ከበድ ያለ ህክምና አግኝተው የኑሮ ደረጃቸው ከወሰዱት የህክምና ዓይነት አኳያ ድጋፍ ለሚሹ ታካሚዎች ራሳቸውን ችለው በየአካባቢያቸው ጤናማ ህይወት መምራት የሚያስችል ሳይንሳዊ የህይወት ክህሎት ስልጠና መስጫ ማዕከል ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡

ጅማሮው ከባድና ፈተናዎች የበዙበት ነበር ይላሉ የፕሮግራሙ ሥራ አስኪያጅ ወ/ሮ በለጥሻቸው ታደሰ፡፡ “ነዋሪዎቹን ማሳመንና አስተማማኝ የስራ ሁኔታና ቦታን ማመቻቸት ባጠቃላይ ከተለመደው አሰራር ወጥቶ አዲሱን አቅጣጫ መዘርጋት አድካሚ ነበር፡፡ አሁን ላይ ደስታ መንደር ከታካሚዎች መቆያነት ወደ አስፈላጊ የህይወት ስንቅ ማግኛ ስፍራነት ተቀይሮ በ16ተኛዙር 8 የፊስቱላ ተጎጂዎች ተገቢውን ስልጠና አግኝተው ወደየማህበረሰባቸው እንዲቀላቀሉ ያስቻለ ሆኗል” ይላሉ ወ/ሮ በለጥሻቸው፡፡

### ለመሆኑ በደስታ መንደር ለታካሚዎች የሚሰጠው ስልጠና ምን ምንን ያካትታል? ከስልጠና መጠናቀቅ በኋላ ያለው ሂደትስ ምን ይመስላል?

በደስታ መንደር የረጅም ጊዜ የህይወት ክህሎት ስልጠና መከታተል የሚችሉት

በፊስቱላ ምክንያት ለአካላዊ፣ ለማህበራዊ፣ ለስነልቦናዊና ለኢኮኖሚያዊ ችግሮች የተዳረጉና በወሰዱት ከመደበኛው የተለየ ህክምና ምክንያት ወደ ማህበረሰቡ ከመቀላቀላቸው በፊት ልዩ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው በባለሙያ የተለዩ ታካሚዎች ብቻ ናቸው፡፡ መስፈርቱን በማሟላት የተለዩት ሰልጣኞች በደስታ መንደር ቆይታቸው እንደነሱ ላሉ አዋቂዎች ማስተማሪያነት በተቀረፀ ሳይንሳዊ ዘዴ ከትንሹ የመግባባትና የመደራደር እስከ ትልቁ የተደበቀ እምቅ እውቀትን በማውጣት በራስ መተማመን የማጎልበት ክህሎቶችን በባለሙያዎች ከ2-3 ወር እንዲሰለጥኑ ይደረጋል፡፡

በተጨማሪም እንደየሰልጣኞቹ ፍላጎት ለገቢ ማስገኛነት የሚያገለግሉ የንግድና የእደጥበባት ክህሎት እንዲሁም በቁጠባ አማካኝነት በትንሽ ገቢ ራስን የማስተዳደር ችሎታን የማዳበር ስልጠናዎች ያገኛሉ፡፡ ከስልጠናው ጎን ለጎንም ወደ ዋናው ሆስፒታል እየመጡ ህክምናቸው እንዲከታተሉ ይደረጋል፡፡

የማገገሚያ ስልጠናውን መጠናቀቅ ተከትሎ በቆይታቸው ያገኙትን ዘርፈ ብዙ እውቀት በተጨባጭ ወደሚተገብሩበት የመልሶ ማቋቋም ምዕራፍ ይሸጋገራሉ፡፡ አንዳንዶቹ እዛው ተወልደው ካደጉበት መንደር ሌሎች ደግሞ በአቅራቢያቸው ከሚገኝ ከተማ በመመለስ መደበኛ ህይወትን ይመራሉ፡፡ ይህ የሆነው ለጤናቸው ቅድሚያ ስለሚሰጥና ኑሮ የሚመሰርቱበት አካባቢ ቢያንስ ውኃ እና የጤና ተቋምን ሊኖረው ስለሚገባ ነው፡፡ በመልሶ ማቋቋም ክፍል አማካኝነት ለእያንዳንዷ ሰልጣኝ በመረጠችው የስራ ዘርፍ እስከ አስር ሺህ ብር (10,000) የሚደርስ የስራ እቅድ ይዘጋጅላታል፡፡ ለክትትል አመቺ እንዲሆን ደግሞ ከየመጡበት አካባቢ ከሚገኝ የመንግስት አካል የመስሪያ ቦታ እንዲያመቻቹላቸው እና ስራቸውንም እንዲከታተሉላቸው የማስተሳሰር ስራ ይሰራል፡፡ የመስሪያ ገንዘቡም አስፈላጊው ቅድመዝግጅት ሲጠናቀቅ በነዚሁ የመንግስት ተቋማት በኩል እንዲደርሳቸውና ስራቸውን እዲጀምሩ ይሆናል፡፡

ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ስራው ከእንከን የፀዳ አይደለም ይላሉ ወ/ሮ በለጥሻቸው፡፡ “በትክክል ተቋቁመው በንግድ ስራቸው ውጤታማ በመሆን ጤናማና ደስተኛ ህይወትን መምራት የቻሉ፣ አንዳንዶቹ ትዳር መስርተው ቤተሰብ የሚያስተዳድሩ የመኖራቸውን ያህል በግለሰቦች ተታለው ወይም ለስራ የተሰጣቸውን ገንዘብ ከዓላማው ውጪ በማጥፋት መልሰው የችግር ህይወት ውስጥ የገቡም አሉ፡፡ ችግሩን ለመፍታትም አንድ ባለሙያ ተመድቦ ታካሚዎቹ ኑሮ በጀመሩበት አካባቢ በመገኘት ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል” ብለዋል ሥራ አስኪያጇ፡፡ የተጠቃሚዎቹ ውጤታማነት የሐምሊንን ሁሉን አቀፍ የተሟላ ህክምና የሚያጎላ እንደመሆኑ የሁሉንም ትኩረት ይፈልጋል ሲሉ ወ/ሮ በለጥሻቸው አክለዋል፡፡

ከ16ኛው ዙር ተመራቂዎች አንዷ የሆነቸው በምርቃት ስነስርዓቱ ላይ ስትናገር፣ “ከፊስቱላ ጋር ለ15 ዓመታት ተሰቃይቻለው፡፡ ይህ ድርጅት ለእኔ ከወላጅ እናትም በላይ ነው፡፡ በተስፋ መቁረጥ ከተጣልኩበት አንስቶ አዳነኝ፤ አሁን ደግሞ ይኸው እራሴን መምራት እንድችል አሰልጥኖ አስመረቀኝ፡፡ ሁላችሁንም አመሰግናለው፤ ለእማዬም ረጅም ዕድሜን እመኛለሁ” ብላለች፡፡

## እናስተዋውቅዎ ---

## የመቱ ሐምሊን ፊስቱላ ማዕከል




ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ የአዲስ አበባውን ዋና ሆስፒታል ጨምሮ በባህርዳር፣ በመቀሌ፣ በይርጋለም፣ በሐረር እና በመቱ ከተሞች ላይ በሚገኙት የህክምና ማዕከላት ለወሊድ ፊስቱላ ተጎጂ ሴቶች ነፃና ሁሉን አቀፍ ህክምና እየሰጠ ይገኛል፡፡ እስካሁንም ከ60 ሺህ በላይ የሚሆኑ ታካሚዎች በእነዚህ ማዕከላት ተገልግለዋል፡፡

የመቱ ሐምሊን ፊስቱላ ማዕከል በኦሮሚያ ክልል፣ በኢሉአባቦራ ዞን መቀመጫ በሆነችው መቱ ከተማ በካርል ሆስፒታል ግቢ ውስጥ እ.ኤ.አ መስከረም 2010 ተገንብቶ አገልግሎት መስጠጥ ጀመረ፡፡

በሐምሊን የግንባታ መርህ ለታካሚዎች ተስማሚና ማራኪ ሆኖ የተገነባው የመቱ ሐምሊን ፊስቱላ ማዕከል አርባ አልጋዎች አሉት፡፡ የታካሚዎች ማረፊያ፣ የምርመራ፣ የቀዶጥገና፣ የማብሰያ፣ የላውንደሪ እና የቢሮ ክፍሎችን ባንድ ላይ የያዘው ማዕከሉ ሰፊና አረንጓዴ የህሙማን መዝናኛ መስክም አለው፡፡ በጥቅሉ ልክ እንደሌሎቹ የሐምሊን ህክምና ማዕከላት የመቱ ሐምሊን ፊስቱላ ማዕከልም በፊስቱላ ሳቢያ የአካል ጉዳት ላጋጠማቸው ታካሚዎች አመቺ ሆኖ የተገነባ ነው፡፡

ከማዕከሉ ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ጥበቡ

አባተ ያገኘነው መረጃ እንደሚያሳየው ማዕከሉ በሙሉ አቅሙ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ከታህሳስ 2010 (እ.አ.አ) እስካሁን ከአንድ ሺህ በላይ ለሚሆኑ ለፊስቱላ ተጎጂ ሴቶች ህክምና ሰጥቷል፡፡ ከእነዚህ መካከል ከሰላሳ በላይ የሚሆኑት ዳግም ወደ ማዕከሉ መጥተው በቀዶጥገና ጤናማ ልጅ ተገላግለው ወደየቤታቸው በደስታ ተመልሰዋል፡፡ በተጨማሪም ማዕከሉ በስሩ ለሚገኙት 14 በሐምሊን ለሚታገዙና የሐምሊን ተመራቂ ሚድዋይፎች ለተመደቡባቸው የመንግስት ጤና ጣቢያዎች የአንቡላንስ አገልግሎት እና ሙያዊ ድጋፍ እየሰጠ ይገኛል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በማዕከሉ የቀዶ ጥገናውን ስራ እየመሩ የሚገኙት በመቱ ካርል ሆስፒታል የሙሉ ሰዓት የፅንስና ማህፀን ሐኪም የሆኑትና በፊስቱላ ቀዶጥገና ህክምና በአዲስ አበባ ፊስቱላ ሆስፒታል አጭር ስልጠና የወሰዱት ዶ/ር ዘሀራ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በማዕከሉ 36 ሠራተኞች የሐምሊን መለያ የሆነውን ታካሚን ያማከለ ሁሉን አቀፍ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ የጋምቤላ አካባቢን ጨምሮ 13 ሚሊየን የሚገመትን ህዝብ እንዲያገለግል የተገነባው የመቱ ሐምሊን ፊስቱላ ህክምና ማዕከል አሁንም አዳዲስና የቆዩ የፊስቱላ ተጎጂ ሴቶችን ተቀብሎ በማከም ላይ ይገኛል፡፡





የሐምሊን ዜና መጽሔት በሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ኮሚዩኒኬሽን ክፍል በየሦስት ወሩ እየተዘጋጀ ለድርጅቱ ሠራተኞች የሚሰራጭ ነው፡፡

አስተያየት ወይም ለዜና የሚሆኑ ሀሳቦች ካለዎት ያድርሱን፡፡

*ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ*
*ኮሚዩኒኬሽን ክፍል*
*ስልክ፡+251 113 720083*
*ፋክስ፡+251 113 726252*
*ኢሜይል፡enquiries@hamlinfistula.org*
*ዌብ ሳይት፡www.hamlinfistula.org*

Hamlin Fistula Ethiopia

*Designed & Printed by Everest Printers*